**የ ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)**

# Ethiopian People’s Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## ለውጥ ስንል ለውጥ ሲሉ!!

ያልነበረ የሌለ ሕገ መንግስት ከኢሕአፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት የተሰጠ መግለጫ

ሕዝባዊ ጸረ ወያኔው ትግላችን ይፋፋም ስንል አዲስ ስርአትን ላረገዘ አሮጌ ስርአት አዋላጅ ከተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግል ውጪ ሌላ ስለሌለ ነው፡፡

በኢሕአፓ  የትግል መንፈስ ተፀንሰን የተደራጀን የኢሕአፓ ልጆች ነንና ከአላማው አላማ ሰርፀናልና ስር ነቀል ኢትዮጵያዊ ለውጥ ያሻል ሲል ኢሕአፓ ኢወክንድም ከዚህ ሌላ መፈክር አያነሳም ምክንያቱም በኢሕአፓ ውስጥ ያለን የወጣት ክንፍ ድርጅት ነንና፡፡

ይህ መነሻችን አድርገን ወደ ላይ ካለው ርዕሳችን ስንጉዝና መግለጫችንን ስናብራራ በኢትዮጵያችን ለለውጥ የምንታገለው ቀጠን ያለ መለሰ ወፈር ባለ መለሰ ለመለዋወጥ ለመተካካት ሳይሆን ይህ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ማለትም የሚኮራበት ስም እና በምንጠየፈው የተግባሩ መጠርያ ወያኔ ከነስረዓቱ ከስሩ ካልተመነገለ በተሸራረፈ የግለሰብና የባዕድ ቡድን በሚለዋወጥ ጉልቻ ጣፋጭ የሆነ የነፃነት አየር እንደማናገኝ ግንዛቤውን ከድርጅታችን ያገኘን የድርጅታችን ወጣቶች መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

በየጎጣችን ተከፋፍለን ኢትዮጵያዊ ራእይ እንዳይኖረን ካደረገን ስርአት ፈልቅቆ በኢትዮጵያ የአንድነት ጎዳና እንድንጓዝ በጨለመው ተስፋችን ብርሃን ላፈነጠቀልን ኢሕአፓ ምስጋና ይሰጠውና ይህንን በሕዝብ ያልተወከለና ሕጋዊ መሰረት የሌለውን ቡድን እንደ መንግስት አልተቀበልነውምና የሌለውንም ህገ መንግስት እንደህግ ተቀብለን ህገ መንግስት ብለን አንጠራውም፡፡

ኢትዮጵያን የበተነና ጨርሶም ከምድረ ካርታ ለማስፋቅ ያመቻቸን ቡድን ለራሱ ተፍጥፎ የሰራውን ሕገ መንግስት ሕገ ወያኔ ነውና መሻሻል ሳይሆን ከስሩ መቀደድ ያለበት መሆኑን አበክረን እንገልፃለን፡፡

ሕጉ ይሻሻል ሳይሆን ስሥርዓቱ ይለወጥ የምንለው ለዚህ ነው፡፡

ወያኔ ሕገ መንግስቱን  ለመጣስ በሚል ዜጋውን የምያምሰው የአንድን  አናሲ የጥቂት ዘረኞችን አገዛዝ ዘላለማዊ ለማድረግ የሚያደርገው መባከን መሆኑን ግንዛቤው ስላለን የሌለ ሕገ መንግስት ምኑ እንደሚጣስ ለራሱ ለጥቂት ደጋፊ ገፋ ሲልም ለባእድ ሞግዚቶች ይገባ ይሁን እንጂ እኛ ግን ድሮም ዛርሬም እንደማንቀበለው አስረግጠን ለማለፍ እንሞክራለን፡፡

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl

ዛሬ የትግላችን አቅጣጫ የስርአቱ ቁንጮዎች በጥላቻ በሽታ ስለተከረከሙ የስርአት ለውጥ ይመጣል ብለን ፍፅም ብዥታ ስለሌለን የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ፀረ ወያኔ ሕዝባዊ ትግላችን በሜዳው ላይ አፉፍመን ወያኔን ሕገ ወያኔንም በስረ ነቀል ለውጥ ኢትዮጵያዊ የሆነ ግዝያዊ ሕዝባዊ መንግስት እስከምቁቁም ኢወክንድ ተመሳሳይ አቁም ካላቸው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ወጣቶች ጋር በመሆን እናት ድርጅታችን ኢሕአፓ የሚከተለውን መርሆ ተከትለን 40 ዓመት በትግልና በመሰዋትነት ያቆዩልንን ትግል እንደምንቀጥል ስንገልፅ በኢትዮያዊ ቃል ኪዳን ነው።

ፀረ ወያኔ ሕዝባዊ ትግላችን ይፋፋም የኢትዮጵያ ትንሳዬ እውን ይሆና ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዓብዮታዊ ፓርቲ ኢሕአፓ 40 ኛው ዓመት እንኩን አደረሳችሁ!

**Joineprpyl@gmail.com** **office- 202 291 5832** **http://eprpyl.com/**
**www.facebook.com/eprpyl**